# በእርዳታ ሱስ የሰከረዉን ወያኔ ማስወገድ የዘላቂ ልማት ቀዳሚ አጀንዳ ነው

የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 58 ርዕሰ አንቅጽ

በስብዓት ነጋ አስቂኝ ዘበዘብ መነሻነት ‹‹ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም›› የተሰኘው የወያኔ ኢኮኖሚ መሠረቱ ሸቀጦችን ማምረት ወይም አገልግሎቶችን ማቅረብ ሳይሆን ከለጋሽ አገሮች የሚገኝ እርዳታን መምጠጥ ነው። የእርዳታ ፍሰት የወያኔ የሕይወት እስትንፋስ ነው። ስለሆነም በችግርኛው ስም የሚመጣው እርዳታ ወደ ወያኔ ቋቶች ያለማቋረጥ መፍሰሱን ማረጋገጥ የሹመኖቹ የሙሉ ጊዜ ሥራ ነው። ወያኔ ምን ያህል በእርዳታ ሱስ የሰከረ ስለመሆኑ በያዝነው ሰኔ ወር ብቻ እንኳን ካስተዋልናቸው ክስተቶች ውስጥ ሶስቱን ብቻ ለአብነት እናነሳለን።

1. ሰኔ 9 ቀን 2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም የዳሬክተሮች ስብሰባ መለስ ዜናዊ ተገኝቶ ባደረገው ንግግር የበለፀጉ አገሮች የልማት እርዳታ ሲሰጡ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ መሻሻልን መጠየቃቸው እና የሚሰጡትም ገንዘብ ከፕሮጀክቶች ጋር መያያዛቸው በእጅጉ አምርሮ ተቃወመ። እነዚህ ‹‹አሳሪ ቅድመ-ሁኔታዎች ናቸው›› በማለትም ተከራከረ። ጉዳዩን ለማክበድም ‹‹የበለፀጉ አገሮች በእርዳታ ሰበብ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነታችንን እየተጋፉ ነው›› አለ። ከዚህ ሁሉ የምሬት ንግግር በኋላ ግን አገሮቹ ያለ አንዳች ቅድመ-ሁኔታ የሚሰጡት እርዳታ መጨመር እንዳለባቸው ተማፀነ። ከሶስት ቀናት በኋላ ሰኔ 12 ቀን ባደረገው ቃለ-መጠይቅ ደግሞ ለኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ምክንያቱ የዓለም ባንክና ለጋሽ አገሮች ናቸው እኛ የሰጠናቸውን የእድገት አሃዝ አምነው ብድር ስላልሰጡን ነው ይኸ ችግር ሊከሰት የቻለው፤ ስለሆነም ጥፋቱ የነሱ ነው አለ። የመለስ እርስ በርሱ የተጣላ ንግግር ትርጉሙ ቢያንስ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ግልጽ ነው - ለጋሽ አገሮችን ‹‹ገንዘባችሁን በርከት አድርጋችሁ ስጡን እንጂ በሰጣችሁን ገንዘብ ምን እንደምናደርግበት አትጠይቁን›› እያላቸው ነው። የመለስን የሰዓታት ንግግር ‹‹ገንዘቡን አምጡ፤ ቁጥጥሩን ግን እርሱት›› በሚል መፈክር ማሳጠር ይቻላል።

2. በያዝነው ሰኔ ውስጥ ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ወገኖቻችን አስቸካይ እርዳታ ይፈልጋሉ። በመላው ዓለም ላይ በደረሰው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ ለኢትዮጵያ የሚሆን የምግብ እርዳታ ማግኘት ቀድሞ ከነበረው ይበልጥ ፈተና ሆኗል። በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የዓለም የምግብ ድርጅት በከፍተኛ ጥረት አሰባስቦ ጂቡቲ ወደብ ያደረሰውን እርዳታ ወደ መሃል አገር ማድረሻ አጥቶ ተቸግሯል። የአጋጣሚ ነገር ሆነና የኤፈርቱ ትራንስ ኢትዮጵያ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት ቀድሞ የወሰደው ማዳበሪያን የማድረስ ኮንትራት አለበት። ሌሎች ድርጅቶች ወይም የግል የጭነት አገልግሎቶች እርዳታውን አድርሰው የኤፈርት ገቢ ከሚጎዳ ድሃው ተርቦ ቢሞት ይመርጣሉና ሰበብ እየፈጠሩ እስካሁን የምግብ ማጓጓዙ ሥራ እንደተጓተተ ነው። የዓለም የምግብ ድርጅት ከሱዳን የትራስፓርት ማጓጓዣዎች የመጠቀምን አማራጭ መፍትሄ ቢያቀርብም መንግሥት ተብዮው ኤፈርት እንዳይጎዳበት ሃሳቡን ተቃወመ። የእርዳታ ማድረስ ሥራ መስተጓጎሉና የረሃቡ መጠንም እየከፋ መሆኑን

ያሳሰበው የድርጅቱ የአዲስ አበባ ቢሮ ስለተሰማው ቅሬታ መግለጫ በመስጠቱ የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስማችን አለአግባብ ጠፍቷልና የዓለም የምግብ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት የአዲስ አበባ ቢሮን መግለጫ ያስተባብል፤ ይቅርታም ይጠይቀን አለበዚያ ግን የእርዳታው እህል ከጂቡቲ አይንቀሳቀስም አለ። ድርጅቱ ዘጠኝ ሚሊዮን ረሃብተኞች በመያዣነት መያዛቸውን እግምት ውስጥ በማስገባት የይስሙላም ቢሆን የወያኔን መንግሥት ይቅርታ ጠየቀ። ‹‹አይጋ›› የተባለው የወያኔ ድረ-ገጽ ደብዳቤው ለጥፎ በደስታ እያቅራራ ነው።

3. በዚሁ ሰኔ ወር የ2002 ዓ.ም የፌደራል በጀት ፀድቋል። ይህ በጀት አንድ ሶስተኛ ያህሉን ገቢ ተስፋ ያደረገው በእርዳታና ብድር ነው። ይህ ብድርና እርዳታን ተማምኖ የተሰላው በጀት ግን ለጦር ሠራዊቱና ለስለላ የሚያወጣው ወጪ ያው እንደተለመደው ከፍተኛ ነው። የታሰበው እርዳታና ብድር ቢገኝ እንኳን የታቀደው ወጪ ከገቢው በአስር ቢሊዮን ብር ይበልጣል።

እነዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሶስት የሰኔ ወር ክስተቶች የሚያስገነዝቡን ወያኔ እና ኩባንያዎቻቸው እየከበሩ ያሉት በድሃው መራብ በመሆኑ የወያኔ አመራር ችጋርን ከኢትዮጵያ የማጥፋት ፍላጎትም ችሎታም ሊኖረው እንደማይችል፤ ወያኔ ረሃብን የፓለቲካ መጠቀሚያ እያደረገ መሆኑን እና የእርዳታው ፍሰት አደጋ ከገጠመው በሚቀጥለው በጀት ዓመት የወያኔ መንግሥት ኢኮኖሚ ተንኮታኩቶ ፈጽሞ ሊቆም የሚችል መሆኑን ነው።

ዋነኛ የገቢ ምንጮቹ በመሆናቸው ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ኢትዮጵያ ከችጋርና ረሃብ መላቀቅ አትችልም። ይህ በእርዳታ ሱስ ናላው የዞረበትን ወያኔን ማስወገድ ችጋርን ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት ለሚደረገው ትግል የመጀመሪያው ወሳኝ ምዕራፍ ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ አገር ወዳድ ወያኔን ማስወድ የድህነት ቅነሳ ትግሉ አቢይ ምእራፍ መሆኑን ተገንዝቦ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የወያኔን የገቢ ምንጮች በማድረቅ ራሱን፣ ቤተሰቡንና አገሩን ያድን እንላለን።

http://www.ginbot7.org/News_Paper/Ginbot_7_Dimts_Issue_No58.pdf